# አዋጁ እንደ ሚስጥር

ከመይሳው

በዚች አጭር ጽሁፍ ውስጥ አንዳንድ የታዛብኳቸውንና መተቸት አለባቸው የምላቸውን ፣ መነሳታቸውም ጠቀሜታ አለው ብዬ ያመንኩባቸውን አሳሳቢ ነጥቦች በተቻለ ለመዳሰስ እሞክራለሁ ፡፡ አብዛኛዎቹ በተናጠል የተተቸባቸው ቢሆኑም በኔ ግላዊ ግንዛቤ ሁለትና ሶስት ነጥቦችን አጣምሬ በማቅረብ ለአንባቢያን ሳበረክት ከንጹ ህሊና በመነሳት መሆኑንም ላሳስብ እወዳለሁ ፣ እነዚህም ነጥቦች ለትግላችን መዳከም ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ከምላቸው ከብዙዎቹ ጥቂቱ ሊሆኑ እንደሚችሉም አምናለሁ ፡፡

በመሰረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች (ድርጅቶች) በሕዝብ ከተመረጡና ሕዝብን እንመራለን ካሉ የሚያገለግሉት ለፓርቲያቸው አባላት፣ ለመረጧቸው ቡድኖች፣ (ሰዎች) ብቻ ተወስኖ የሚቀር እንዳልሆነ ለድርጅት ተብዬዎቹ መጠቆም ጨዋታው ሌላ ካልሆነ በቀር *"እናት ለልጇ ምጥ አስተማረች"* እንዳይሆንብኝ እሰጋለሁ፡፡ እንግዲህ ሕዝብን የሚያገለግሉ ከሆነ ፣ ለሕዝብ አገልጋይ ነን ካሉ አንድ ግለሰብ ወይንም ቡድን የነሱ ደጋፊያቸው ሆነም አልሆነም እንዲብራራልኝ እፈልጋለሁ ብሎ ለሚያነሳው ጥያቄ በአግባቡና በወቅቱ አጥጋቢ ምላሽ መስጠት የግድ ይላል፣ ይህን ለማድረግ ፈቃደኝነቱ ከሌለ ታጥቦ ጭቃ "አልሸሹም ዞር አሉ" አይነት የትግል አዝማሚያ እየተካሄደ ነው ብል አልተሳሳትኩም እላለሁ ፣ ስለሆነም ብዙ ከመድከምና ከመሀል መንገድ ደርሶ እንደገና ሁኔታውን ለማረም ወደኋላ ከመመለስ በጊዜው ትኩረት ተሰጥቶት እርምት እንዲደረግ ለማሳሰብ ነው፡፡

በተለይ በዚህ በ (Diaspora) ያለውን ትግል በግንባር ቀደምተኝነት እንመራለን እያሉ ከላይ ታች የሚባዝኑትን ሁለት ግለስቦች እና እንዲሁም ጋሻጃግሬዎቻቸው እንዲገነዘቡልኝ የምወደው አንድ ነገር አለ ይኸውም ነገ በለስ ከቀናቸውና ለስልጣን ከበቁ እንመራታለን ከሚሏት የኢትዮጵያ ሕዝብ መሀከል አንዱ ስለሆንኩና እንደማንኛውም ሐገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በሐገሬ ጉዳይ ስለሚያገባኝ ዛሬ እነሱ እቶ የተባሉና የተከበሩ ናቸው እነሱን መተቸት ትግሉን ማዳከም ይሆናል ብለው ለሚተቹኝ ምስኪኖች ፣ መልሴ እራሳችሁን አታሞኙ "ሲ" ን ፣ በ "ላ" ልተካ አልታገልም እነሱ በያገባኛል የሚያቦኳት ኢትዮጵያ የኔም ኢትዮጵያ ነች ፣ እነሱና ደጋፊዎቻቸው የበህር ልጅ ሌላው ግን የንጀራ ልጅ እንዳልሆነ ሁሉም ሊረዳው ይገባል በማለት አስቀድሜ ልመልስላቸው እወዳለሁ ፡፡

እነዚህ ሁለት ግለሰቦች በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በምርጫም ይሁን በያገባኛል ወይም በውከላ ዛሬ በግንባር ቀደምተኝነት ትግሉን እንመራለን እስካሉ ድረስ ፣ ወያኔን ጸረ ዲሞክራሲና አፋኝ ነው ብለው የሚወነጅሉ ከሆነ እነሱ የወያኔ ካርቦን ኮፒ አለመሆናቸውን ለማሳየትና ለማሳመን ወያኔ የሚሰራውን ከመተግበር ይልቅ ተቃራኒውን በመስራት እምነት እንዲጣልባቸው አላደረጉም ፣ ይህንንም ያልኩት ያለ ምክንያት አይደለም ፣ እነኚህ ሁለት ግለሰቦች ከበርካታ ኢትዮጵያዊያን አንዳንድ ጉዳዮችን እንዲያብራሩላቸው በተደጋጋሚ ጥሪ ቢቀርብላቸው አሻፈረን በማለት እምቢተኝነታቸውን አሳይተዋል ፣ ይህም ሊሆን የቻለው እንዲብራራላቸው ጥሪ ያደረጉላቸው ክፍሎች (ቡድኖች) በአቋማቸው ጠንካራና ሰለፖለቲካውም ጥሩ ግንዛቤ ያላቸው በቀላሉ ሊወናበዱና ሊታለሉ

የማይችሉ በስሜታዊነት በ (emotion) ን የሚነዱ ሳይሆኑ በ (principle) የሚመሩ ጠንካራ የሕብረተሰቡ ታጋይ ክፍሎች በመሆናቸው የጠለቀና የረቀቀ ጠንካራ ጥያቄዎች ሊያቀርቡ እንደሚችሉ አስቀድመው ስላወቁት ከዚያ ለመሸሽ ያለ የሌል ምክንያት በመደርደር አንዳንዴም የናቴ መቀነት አደናቀፈኝ በማለት በየጊዚው ምክንያት በማቅረብ በእንግድነት ቀርበው መልስ የተጠማውን ሕብረተሰብ በአግባቡ ለሚያንገበግበው ጥያቄ ተገቢውን መልስ  በመስጠት አይምሮው እረፍት እንዲያገኝ ፈቃደኞች አልሆኑም ፣ ለሐገሩ በቅንነት የሚለፋውንና የሚንገበገበውን ኢትዮጵያዊ ከወያኔ ባላነሰ መልኩ በማግለል ጸረ ዲሞክራሲ መሆናቸውን ባድራጎታቸው በተዘዋዋሪም ይሁን በቀጥተኛ መንገድ አስመስክረዋል፡፡

በአንፃሩ ግን የኛን መርሆ ይደግፋሉ የምንነግራቸውን ሁሉ እንደ እስፖንጅ መጠው አሜን አሜን ብለው አወደሰውና መርቀው ያሰናብቱናል የሚሏቸ ክፍሎች ውስጥ ግን ነጋ ጠባ መመላለሳቸው ብቻ ሳይሆን ምናልባት ክፍሉ ውስጥ ሁኔታዎች ተፈጥረው እኛ እንድንመጣላቸው ይፈልጉ ይሆናል በማለት ስልካቸውን ጆሯቸው ላይ ለጥፈው እንደሚውሉ ታዝቢያለሁ ፣ አለቀጠሮ ወዲያው ተደውሎ ሲቀርቡና ውዳሴያቸውን ተቀብለው ወንድሞቼ ፣ ልጆቼ ፣ እህቶቼ ብለው ሸውራራውን አይኑን አጥፍተውለት ሲነጉዱ ለመታዘብ በቅቻለሁ ፣ ይህም ማጋነን ሳይሆን ያየሁትና የምመሰክረው ጉዳይ ነው ፣ አይመቹንም ወይንም ወጥረው ይይዙናል የሚሏቸውን ክፍሎች ግን ሰብሰባ አለን ፣ ስራ አለን ፣ ወዘተ... በማለት ዱቤ ከልላቸውን እየተከናነቡ ድብብቆሹን ተያይዘውታል ፡፡ ያልገባኝ ነገር ቢኖር አንድ ፓርቲ አላማዬ ትክክለኛ ነው ፣ አብዛኛው ሕዝብ ይደግፈኛል ብሎ ካመነ ድብብቆሹን ምን አመጣው? በራሱ የሚተማመን ግለሰብም ሆነ ድርጅት የሚደግፏቸውንና አሜን አሜን የሚሏቸው ዘንድ እየተመላለሱ ጋሽዬ ፣ ጋሽዬ፣  እያሉ ስላቆላመጥዋቸው ውሎና አዳራቸውን ከነኚሁ ጋሻ ጃግሬዎች ቤት ማድረጉ ውዳሴ ከንቱን ተቀብሎ መመለሱ ትግሉን የቱ ላይ ነው ያራመደውና የረዳው?  በራሱና በአቋሙ የሚተማመን ድርጅትም ሆነ ግለሰብ ተቃዋሚ የሚላቸው ዘንድ ቀርቦ ተቃዋሚዎቹን የተሳሳተ መንገድ እንደያዙ ማስተማርና ማስረዳት የራሱን አላማ በተገቢው በማብራራትና በማሳመን በተቃዋሚ ዘርፍ ያሉትን ወደሱ ጎራ እንዲመጡ ጥረት ያደርጋል እንጂ የሚሸሹና የሚርቁት ከሆነ አንድም በራሳቸው ላይ እምነት የላቸውም ሌላው ሊሆን የሚችለው ደግሞ የደበቁትና እንዳይታወቅባቸው የፈሩት ነገር አለ ማለት ነው ፣ ይህንን ለመረዳት ደግሞ ጠንቋይ መቀለብ አያሻም ፣ ይህን አይነት የማግለልና የመሸሽ ጨዋታ መጨረሻው ተቃዋሚውን ወገን ወይንም ጥያቄ አለኝ የሚለውን ቡድን የበለጠ እንዲጠረጥርና መልሰው ወደምንታገለው አይነት ስርአት ሊመሩን ነው በሚል ጥርጣሬ ይበልጥ እንዲታገላቸው ይገፋፋል ስለሆነም እርስ በእርስ የሚደረገው ትግል በከፋ ሁኔታ ይጋጋላል ለዚህም ተጠቃሚው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይሆን ወያኔ ይሆናል ፣ እንግዲህ እዚህ ላይ ይህ አይነት ሁኔታ እንዲፈጠር ያደረገው ማን ነው? የምንፈርጀውስ ከየትኛው ጎራ ይሆናል? መልሱን ለአንባብያን እተወዋለሁ፡፡

ጉዳዩን ለመቋጨት ወያኔን እንቃወማለን የሚሉትን የተለያየ አመለካከት ያላቸውን የሕብረተሰብ አካሎች ለማቀራረብና ቅራኔው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋ እንዳይሄድ ጥያቄ አለን በሚሉ ክፍሎች ውስጥ በመቅረብ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እውነቱን በማሳወቅ የታሪክ ግዴታቸውን እንዲወጡ ጥሪዬን አቀርባለሁ ፣ ለዚህ ቅን ተግባር ግን ፈቃደኝነትን ካላሳዩ ለትግሉ መዳከም ስውር ተልእኮ አላቸው ለማለት

እደፍራለሁ ፡፡ ለዚህም ተግባራቸው በታሪክ ተጠያቂ ከመሆን እንደማያመልጡ ሊጠራጠሩ አይገባቸውም ፡፡

ሌላው ሳላነሳው የማላልፈው አሳዛኝና አሳሳቢ ጉዳይ ደግሞ እነዚሁ ሁለት ግለሰቦች የኛ የሚሏቸው ክፍል ውስጥ የሚካሄደው ኢትዮጵያዊነት የጎደለው ስነምግባር ነው፡፡ በኔ ግምገማ እነዚህ ክፍሎች ቀጥተኛ ያልሆነ ከነዚሁ ሁለት ግለሰቦች ወይንም የግለሰቦቹ እንመራዋለን በሚሉት ድርጅት አማካኝነት ለዚህ ክፍል ከፍተኛ የሆነ ድጋፍና ማበረታታት እንደሚደረግለት አልጠራጠርም ይህም የድጋፍ መስጠቱ ጉዳይ  በብራስልስ ውስጥ በተደረገው ስብሰባቸው ላይ ተነስቶ እንደነበር ተዘግቧል ፡፡ ይህ ክፍል እንደዛሬዎቹ የድል አጥቢያ አርበኞችና ከኛ በላይ አዋቂ ላሳር እንደሚሉት ግለሰቦች ሳይሆኑ በትግል አቋማቸው እንደሌሎቹ አጠያያቂ ሳይሆኑ በሳት የተፈተኑ ሐገር የሚያውቀውና የተመሰከረላቸው  ብርቅዬ የኢትዮጵያ ባለውለታዎች ለሐገራቸው ባላቸው  እውቀትና ጉልበት ህይወታቸውን በሙሉ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ በመታገልና በማገልገል ከብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ በላይ ከፍተኛ መስዋእትነትና አስተዋጽኦ ያደረጉ የተከበሩ ኢትዮጵያዊያን ምሁራንና አዛውንት አባቶች የሚዋረዱበት ፣ የሚሰደቡበት ፣ የሚንጓጠጡበት ክፍል ነው ፡፡ ያም ሆኖ ግን ግለሰቦቹ ተሰደብን ተዋረድን ሳይሉ በተደጋጋሚ ለሚደረግላቸው ጥሪ ልንሰደብ ለምን ብለን ሳይሉ ካላዋቂነት የተሰነዘረ መሆኑን በመረዳት ጥሪውን በማክበር እውቀታችሁን ከማካፈል ቦዝነው አያውቁም ፣ ለረጅም አመት ያካበቱትን የሰራና የትግል ተለምዶ ከማካፈል ወደኋላ አልላሉም ፣  ለዚህም አድራጎታቸው ትልቅ ምስጋናና ክብር ሊሰጣቸው ይገባል እላለሁ ፡፡ እዚህ ላይ ለመጠቆም የምወደው ከላይ የጠቀስኳቸው ሁለት ግለሰቦች እውነት ለኢትዮፓጵያና ለሕዝቧ አሳቢ ነን ካሉ እነዚህ ምሁርና አዛውንት ኢትዮጵያዊያን ላመኑበት አላማ በነሱ ተከታዮች እየተሰደቡም ቢሆን እንኳ አላማቸውን ለማስረዳትና ለማሳመን ከሚያደርጉት ጥረት ትልቅ ትምህርት ሊወስዱ ይገባቸዋል ፡፡

በተጨማሪ መነሳት አለበት የምለው በነዚሁ ግለሰቦች የሚካሄደው የኦነግን አመለካከትና አላማ በስማ በለው እየመጡ የሚነግሩን ጉዳይ ነው ፣ ኦነግ እናንተ እንደምተሉት አይደለም ፣ ኢትዮጵያዊ ነው ፣ በውስጣቸው አክራሪዎች ስላሉ ነው ፣ ወዘተ… የመሳሰሉት የውክልና ስራ ከምን የመነጨ እንደሆነ ለማወቅ ተቸግሬአለሁ ፣ ለመሆኑ የኦነግ ሰዎች ስለራሳቸው አቋምና ምኞት በድሕረገፃቸውና በየስብሰባው እየነገሩን የነኚህ ሁለት ግለሰቦች ማስተባበል ምን ታስቦና ማንን ለማደናገር ነው? በመሆኑም ከዚህ የወሬ ሽማኔነት ተግባር ቢቆጠቡ መልካም ነው ፣ ኦነግ ወደ ኢትዮጵያዊነት መጥቻለሁ ግንጠላ የሚለወን ተረት ፣ ተረት ትቻለሁ ብሎ ካለ በድሕረገጹ ፣ በሚዲያ ፣ እንዲሁም በሚደረጉት ስብሰባዎችና ጥሪ በሚደረግላቸው ክፍሎች ሁሉ በመቅረብ ስለራሳቸው እራሳቸው ይናገሩ "ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው" ስለሚባል ሰለ እገሌ ፣ እገሌ ራሱ ይናገር ፣ እናንተ ስለራሳችሁ ብቻ ተናገሩ ፣ ምነው ይህ አይነቱ የመከላከል ተግባር ኢትዮጵያዊ ለሆኑ ድርጅቶችና ወገኔ ለሚላችሁ ቢሆን እንዴት በኮራንባችሁ ነበር?

በመደምደሚያዬ ላይ አንድ ልበልና ለሀተታዬ እልባት እሰጠዋለሁ ፣ ከላይ የጠቀስኳቸው ጥቂት አሳሳቢ ጉዳዮችና ሌሎችም በርካታ ምክንያቶች ተዳምረው ዛሬ ለደረስንበት አሳዛኝ ሁኔታ በቅተናል ፣ ሆኖም "ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም" ቢባልም ለሚመጣውም ክረምት ቤት ሳይሰሩ መቅረቱ ግን ቂልነት ወይንም ድንቁርና ይሆናል ስለሆነም ካለፈው ስህተት በመማር ወደፊት መሄድ የሚያስችለን ዋነኛና ቁልፍ የሆነ ብዬ የማምነው አስኳሉ  በሕብረቱና በቅንጅት መሀከል

ተቀራርቦ ለመስራት ያላስቻላቸው ጉዳይ ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግልጽ የጠራና ምላሽ መስጠት ስላልቻለ ፣ በሬድዮ ፣ በድሕረ ገጾች ወይንም በፓል ቶኮች ውስጥ እየመጡ ለማስረዳት ከመሞከር ይልቅ ከሁለቱም ድርጅቶች ቢያንስ ቢያንስ ሁለት ፣ ሁለት ግለሰቦችን በመወከል ትልቅ ሕዝባዊ ስብሰባ በመጥራት በሁለቱ ድርጅቶች መሀከል አብረው እንዳይሰሩ እንቅፋት የሆነው ሚስጥራዊ ጉዳይ አደባባይ ወጥቶ ሕዝብ የሁለቱንም ድርጅቶች ለዩነትና አንድነት መገምገም እንዲችል እድል ተሰጥቶት ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን በማቅረብ የሚታረቀውን እንዲታረቅ የማይታረቁ ሁኔታዎች ካሉም እንዴት ተቻችለው አንዱ የአንዱን አመለካከትና አስተያየት ሳይጋፋ በመከባበር እንዴት አብረው ሊሰሩ እንደሚችሉ መፍትሄ ከብዙሀኑ ሊፈልቅና ሊቀርብ ይችላል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ ፡፡ ሕዝብ ባለበት ፣ ታዛቢ ባለበት ፣ ጠያቂ ባለበት ፣ ግልጽ ስብሰባ እንጂ ሁለቱ ድርጅቶች ብቻ በግል ተሰብስበው ለሕዝብ ግልጽ ባልሆነ መድረክ ለመስማማት የሚደረገው ጥረት ውጤት ያመጣል የሚል እምነት የለኝም ፣ ይህንን ለማለት ያበቃኝ በሁለቱ ድርጅቶች መሀከል ለሕበረተሰቡ ግልጽ ያልሆነ ነገር ግን አገር ያወቀው ፀሀይ የሞቀው አንዱ ባንዱ ላይ ጥሩ ያልሆነ አመለካከት እንዳለ ስለተገነዘብኩ ነው ፣ አዋጁ እንደሚስጥር ተያዘ እንጂ ፡፡ ለሕብረተሰቡ ግልጽ ያልሆነ መቃቃር በመሀላቸው እስካለ ድረስ የሁለቱ ድርጅቶች አመራር አባላት ብቻ ተሰባስበው ከስምምነት ሊደርሱ ይችላሉ የሚል ቅዠት የለኝም ፣ ለኔ እንደግለሰብ ግልጽ ያልሆነ መቃቃር አለ ብዬ ስለማምን ሁሌም ከስብሰባው በኋላ አንዱ ካንዱ ገኖ ለመታየት እኛ እንዲ ስንል እነሱ እንዲህ አሉ እየተባባሉ ጣት መተቋቆሙ አይቀሬ ስለሆነ ያደባባዩ መተራረም ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ቢደረግ ለሁላችንም ይበጃል እላልሁ፡፡

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ